መልእክት አሥራ-ሁለት

## ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መከናወን በመንፈሳዊ ልምምዳችን መሠረት
## የአዲሱን ኪዳን ይዘቶች መለማመድ እና መደሰት

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ኤር. 31፡31-34፤ ዕብ. 8፡8-12፤ ሮሜ 8፡2፣ 28-29፤ 12፡1-2

**I. አዲሱን ኪዳን በተመለከተ ኤርሚያስ በሚተነብየው ሐቅ መሠረት፣ የኤርሚያስ መጽሐፍ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍም ጭምር የሆነ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ተደርጎ መቆጠር ይችላል፤ የአዲሱን ኪዳን ይዘቶች በእግዚአብሔር እንደተሰጡን የውርስ ኑዛዜዎች ማየት እና የራሳችን አድርገን መውሰድ ያስፈልገናል—ኤር. 31፡31-34፤ ዕብ. 8፡8-12፦**

ሀ. በአዲሱ ኪዳን አራት በረከቶች ቃል ተገብተዋል፦

1. ለአመፃችን ስርየት እና የኃጢአቶቻችን መረሳት (ይቅር መባል)—ቁ. 12።
2. መለኮታዊው ሕይወት ወደ ውስጣችን በመካፈሉ የሕይወትን ሕግ መካፈል—ቁ. 10።
3. እግዚአብሔር አምላካችን የመሆኑ እና እኛም የእርሱ ሕዝብ የመሆናችን እድል—ቁ. 10።
4. እርሱን እንደ ውስጣዊው የሕይወት መንገድ ለማወቅ የሚያስችለን የሕይወት አገልግሎት—ቁ. 11።

ለ. የኃጢአቶች ይቅር መባል የእግዚአብሔርን ዓላማ የማሳኪያ የከንውን ሂደት ብቻ ስለሆነ፣ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የኃጢአቶች ይቅር መባልን በስተመጨረሻ ያስቀምጠዋል፤ ሆኖም ግን፣ በመንፈሳዊ ልምምዳችን መሠረት፣ ይቅር ከመባል የሚመጣውን መንጻት በመጀመሪያ እናገኛለን፤ ቀጥሎም እግዚአብሔርን እንደ የሕይወት ሕግ እንደሰተዋለን፣ በሕይወት ሕግ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንሆናለን፣ ውስጣዊ በሆነ መንገድም የጠለቀ እግዚአብሔርን ማወቅ ይኖረናል—ተዛ. ቁ. 12።

**II. "ዓመፃቸውን እምራቸዋለሁና፥ ኃጢአታቸውንም ደግሜ አላስብም"—ቁ. 12፤ ኤር. 31፡34፦**

ሀ. ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ለማሟላት የእግዚአብሔርን የጽድቅ ጥያቄዎች በመመለስ ያስታርቀን ዘንድ ኃጢአቶቻችንን አስተሰረየ—ዕብ. 2፡17።

ለ. ሕይወታዊ ማዳኑን ያለማቋረጥ ለመደሰት ከእግዚአብሔር ጋር በማያቋርጥ ኅብረት ውስጥ እንቆይ ዘንድ ክቡር የሆነው እና ለሁሉ-ፍቱን የሆነው የክርስቶስ ደም ችግሮቻችንን በሙሉ ይፈታል—1 ዮሐ. 1፡7-9፤ 2፡1-2፦

1. በእግዚአብሔር ፊት፣ የሚቤዠው የክርስቶስ ደም ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ለዘላለም አንጽቶናል (ዕብ. 9፡12፣ 14)፣ የዚያም ማንጻት ፍቱንነት መደገም አያስፈልገውም።
2. ሆኖም ግን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ኅብረት ሕሊናችን በመለኮታዊው ብርሃን አብርሆት ሲያገኝ በሕሊናችን ውስጥ ደግሞ ደጋግሞ የጌታ ክቡር ደም የማያቋርጥ ማንጻት አስቸኳይ ትግበራ ያስፈልገናል።
3. እግዚአብሔር አንዴ ይቅር ካለን፣ ኃጢአቶቻችንን ከሀሳቡ ያጠፋቸዋል ደግሞም አያስታውሳቸውም፤ የኃጢአቶች ይቅርታ ማለት ከእግዚአብሔር ጽድቅ ቅጣት አርነት እንወጣ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት በእኛ ላይ የተጫነ ኃጢአት መወገድ ማለት ነው—ዮሐ. 5፡24፦
   ሀ. እግዚአብሔር ኃጢአቶቻችንን ይቅር ሲል፣ የሠራናቸው ኃጢአቶች ከእኛ እንዲርቁ ያደርጋል—መዝ. 103፡12፤ ዘሌ. 16፡7-10፣ 15-22።
   ለ. የእግዚአብሔር ኃጢአቶቻችንን ይቅር ማለት ከእርሱ ጋር በተመለሰልን ኅብረት እርሱን የመፍራታችንን እና የመውደዳችንን ውጤት ያመጣል—መዝ. 130፡4፤ ሉቃ. 7፡47።

ሐ. ክቡር የሆነው የክርስቶስ ደም እግዚአብሔርን ያረካል፣ የአማኞች ወደ እግዚአብሔር መግባት ነው፣ የጠላትንም ክሶች በሙሉ ድል-ይነሣል (ዘጸ. 12፡13፤ ኤፌ. 2፡13፤ 1ጴጥ. 1፡18-19፤ ዕብ. 10፡19-20፣ 22፤ 9፡14፤ 1 ዮሐ. 1፡7፣ 9፤ ራእ. 12፡10-11)፤ በተጨማሪም የጌታ ክቡር ደም በዘሌዋውያን 16 ሊቀ ካህናቱ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በገባበት ደም የተመሰለው የዘላለማዊው ኪዳን ደም ነው (ማቴ. 26፡28፤ ዕብ. 13፡20)፦

1. የኪዳኑ ደም እግዚአብሔርን እንድንደሰት እና በእርሱ እንድንሰረጽ ወደ ተግባራዊው ቅድስተ ቅዱሳን (ዕብ. 10፡19-20)፣ ወደ መንፈሳችን (ኤፌ. 2፡22፤ 2 ጢሞ. 4፡22) ውስጥ እንድንገባ ያስችለናል።
2. በአዲስ ኪዳን ባለው መገለጥ መሠረት፣ በኪዳኑ ደም ወደ እግዚአብሔር መገኘት ውስጥ ብቻ አንመጣም—ወደ ራሱ ወደ እግዚአብሔር ውስጥም ጭምር እንመጣለን፤ የሚቤዠው እና የሚያነጻው ደም ወደ እግዚአብሔር ውስጥ ያመጣናል!
3. የኪዳኑ ደም በዋናነት እግዚአብሔር ለድሰታችን የሆነ እድል-ፈንታችን ይሆን ዘንድ ነው—ተዛ. መዝ. 27፡4፤ 73፡16-17፣ 25፤ 1 ቆሮ. 2፡9፤ ዕብ. 10፡19-20።

4. በመጨረሻም፣ የክርስቶስ ደም እንደ የአዲሱ ኪዳን ደም (ማቴ. 26፡28፤ ሉቃ. 22፡20) የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ አዲሱ ኪዳን የተሻሉ ነገሮች ውስጥ ያስገባል፣ ይኸውም እግዚአብሔር ለሕዝቡ አዲስ ልብ፣ አዲስ መንፈስ፣ የእርሱን መንፈስ፣ ውስጣዊውን የሕይወት ሕግ (እግዚአብሔር ራሱን ከተፈጥሮው፣ ከሕይወቱ፣ ከባሕርያቱ እና ከሰናይ ባሕርያቱ ጋር የሚያመለክተውን)፣ እና እግዚአብሔርን ለማወቅ የሆነ የሕይወት ችሎታን የሚሰጥበት ነው (ኤር. 31፡33-34፤ ሕዝ. 36፡26-27፤ ዕብ. 8፡10-12)።
5. ከፍተኛና የመጨረሻ በሆነ መልኩ፣ የአዲሱ ኪዳን፣ የዘላለማዊው ኪዳን ደም (13፡20) የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዲያገለግሉት ያስችላቸዋል (9፡14) እንዲሁም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለአሁን እና ለዘላለም (ራእ. 7፡14፣ 17፤ 22፡1-2፣ 14፣ 17) እንደ እድል-ፈንታቸው ወደ እግዚአብሔር ሙሉ ድሰታ (የሕይወት ዛፍ እና የሕይወት ውኃ) ውስጥ ይመራቸዋል።

**III. "ሕጌን በአእምሯቸው አኖራለሁ፣ በልባቸውም እጽፈዋለሁ"—ዕብ. 8፡10 (አ.መ.ት)፤ ኤር. 31፡33፡-**

ሀ. የአዲሱ ኪዳን ማዕከል፣ ማዕከላዊነት፣ ውስጣዊው የሕይወት ሕግ ነው፤ የመለኮታዊው ሕይወት ሕግ፣ የሕይወት መንፈስ ሕግ (ሮሜ 8፡2) የመለኮታዊው ሕይወት ያለሰው ቁጥጥር የሆነ መርህ እና ቅጽበታዊ ኃይል ነው።

ለ. እንደ "ሳይንሳዊ" ሕግ፣ ያለሰው ቁጥጥር እንደሚሠራ መርህ፣ በመንፈሳችን የተተከለ የሕይወት መንፈስ ሕግ ለመሆን ሦስታንዱ አምላክ በተሠግዎ፣ በመሰቀል፣ በትንሣኤ እና በዕርገት ሂደቶች አልፏል—ቁ. 2-3፣ 11፣ 34፤ 16።

ሐ. ዛሬ የእግዚአብሔር ግንኙነት ከእኛ ጋር ሙሉ በሙሉ የተመሠረተው በሕይወት ሕግ ላይ ነው፤ ሁሉም ሕይወት ሕግ አለው እንዲያውም ሕግ ነው፤ የእግዚአብሔር ሕይወት ከፍተኛው ሕይወት ነው፣ የዚህም ሕይወት ሕግ ከፍተኛው ሕግ ነው—ተዛ. ምሳ. 30፡19፤ ኢሳ. 40፡30-31።

መ. ርዕሱ የሕይወት መንፈስ ሕግ (ሮሜ 8፡2) የሆነው ሮሜ 8 የመላው መጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት እና የአጽናፍ-ዓለም ማዕከል ተደርጎ መቆጠር ይችላል፤ ስለዚህ፣ ሮሜ 8ን እየተለማመድን ከሆነ፣ በአጽናፍ-ዓለም ማዕከል ውስጥ ነን፡-

1. እኛን ከኃጢአት እና ከሞት ሕግ አርነት ያወጣን ዘንድ እግዚአብሔር አሁን በውስጣችን ያለሰው ቁጥጥር፣ ቅጽበታዊ እና የማይታወቅ በሆነ መንገድ እንደሚሠራ ሕግ አለ፤ ይህ በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ ካሉ እጅግ ትልቅ ግኝቶች፣ ምለሳዎች ውስጥ አንዱ ነው።
2. ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መከናወን በሕይወት መንፈስ ሕግ አሠራር ወደ ማንነታችን ውስጥ የሚታደለውን ሕይወት እንደሰታለን—ኤር. 31፡33፤ ዕብ. 8፡10፤ ሮሜ 8፡2-3፣ 10፣ 6፣ 11።
3. በሮሜ 8 ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ድሰታ በሮሜ 12 ወዳለው ወደ የክርስቶስ አካል እውነታ ውስጥ ያስገባናል፤ ይህ ሕግ በውስጣችን የሚሠራው በአካሉ ውስጥ እና ለአካሉ ስንኖር ነው—8፡2፣ 28-29፤ 12፡1-2፣ 11፤ ፊልጵ. 1፡19።

ሠ. መለኮታዊ ሕይወቱን ወደ ውስጣችን በማካፈል፣ እግዚአብሔር የዚህን ከፍተኛ ሕይወት ከፍተኛ ሕግ (በነጠላ ቁጥር) በመንፈሳችን ውስጥ ያስቀምጣል፣ ከዚያም በመነሣት ወደ የውስጥ ክፍሎቻችን፣ ወደ አእምሯችን፣ ስሜታችን እና ፈቃዳችን ይሰራጭ እና ብዙ ሕጎች ይሆናል (በብዙ ቁጥር—ዕብ. 8፡10)፡-

1. በውስጣችን የዚህ ሕግ መሰራጨት ወደ ውስጣችን መተላለፉ ነው (8፡10፣ 6)፣ ወደ ውስጣችን መተላለፉ ደግሞ በውስጣችን ተቀርጾ መጻፉ ነው (2 ቆሮ. 3፡3)፤ ጌታ ሲሰራጭ፣ ወደ ውስጣችን ሲተላለፍ እና በውስጣችን ተቀርጾ ሲጻፍ ሳለ፣ የአዳምን አሮጌ ንጥረ-ነገር ከእኛ ይቀንሰዋል፣ የክርስቶስን አዲስ ንጥረ-ነገር ወደ እኛ ውስጥ ይጨምረዋል፣ ይህም በገንባ-አፍራሽ ቅንባሮ የሕይወት ልውጠትን ያከናውንልናል—ቁ. 18።
2. በውስጣችን ባለው በሕይወት ሕግ መሥራት እና መሰራጨት፣ እግዚአብሔር በሕይወት፣ በባሕርይ እና በመገለጥ ከእርሱ ጋር አንድ ዓይነት ያደርገናል፤ በሕይወት ሕግ አሠራር የእግዚአብሔርን በኵር ልጅ መልክ እንመስላለን—ሮሜ 8፡2፣ 29።

ረ. ከእርሱ ጋር ግንኙነታችንን ስንጠብቅ፣ ከእርሱ ጋር መደበኛ ግንኙነት ሲኖረን የሕይወት ሕግ፣ የሕይወት መንፈስ ሕግ፣ ያለሰው ቁጥጥር፣ ቅጽበታዊ፣ እና ጥረት በሌለው መንገድ ይሠራል—ፊልጵ. 2፡12-13፤ ሮሜ 8፡2፣ 4፣ 6፣ 13-16፣ 23፤ 1 ተሰ. 5፡16-18፡-

1. ከራሳችን ትግል እና ጥረት መቆም አለብን—ገላ. 2፡20፤ ተዛ. ሮሜ 7፡15-20፡-
   ሀ. ኃጢአት ሕግ እንደሆነ እና ፈቃዳችን ይህንን ሕግ ፈጽሞ ድል-መንሣት እንደማይችል ካላየን፣ በሮሜ 7 ውስጥ ተጠምደን ተይዘናል፤ ወደ ሮሜ 8 መቼም ቢሆን አንደርስም።
   ለ. ጳውሎስ ለማድረግ ደግሞ ደጋግሞ ወሰነ፣ ውጤቱ ግን ተደጋጋሚ ውድቀት ነበር፤ ሰው ማድረግ የሚችለው ምርጡ ነገር ቁርጠኛ ውሳኔ ማድረግ ነው—7፡18።

ሐ. በውስጣችን ኃጢአት እንቅስቃሴ-አልባ ሲሆን፣ እንዲሁ ኃጢአት ብቻ ነው፣ ነገር ግን መልካምን ለማድረግ በመወሰናችን ሲነሣሣ፣ "ክፉ" ይሆናል—ቁ. 21።

መ. በመወሰን ፈንታ አእምሯችንን በመንፈስ ላይ ማድረግ እና በመንፈስ መሠረት መመላለስ አለብን—8፡6፣ 4፤ ፊልጵ. 2፡13።

2. ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረት ለማስቀጠል እንደ ሕይወት መንፈስ ሕግ በውስጥ ከሚያድረው፣ ውስጣችን ከተተከለው፣ ያለሰው ቁጥጥር ከሚሠራው እና በውስጥ ከሚሠራው እግዚአብሔር ጋር በጸሎት እና በጥገኝነት መንፈስ፣ የጌታን ስም በመጥራት እና ቃሉን እየጸለይን-በማንበብ መተባበር አለብን—ሮሜ 10፡12-13፤ 1 ተሰ. 5፡17፤ ኤፌ. 6፡17-18፡-

ሀ. ክርስቶስን እንደ የሕይወት ሕግ የመለማመጃው ምሥጢር ነገሮችን ሁሉ ለማድረግ ኃይል በሚሰጠን በእርሱ ውስጥ መሆን ነው፣ እንዲሁም በእርሱ ውስጥ የመሆኛው ምሥጢር በመንፈሳችን መሆን ነው—ፊልጵ. 4፡13፣ 23።

ለ. በመንፈሳችን ለመኖር፣ በፊቱ ገጽታ (በመገኘቱ) ውስጥ ሰጥሞ ለመቆየት፣ በውብቱ ፈጽመን ለመሞላት፣ እና ልቀቱን ለማንጸባረቅ ከጌታ ጋር ኅብረት ለማድረግ በመጸለይ ጌታን ትኩር ብለን ለመመልከት ጊዜ መውሰድ አለብን—2 ቆሮ. 3፡16፣ 18፤ ተዛ. ማቴ. 14፡23።

ሰ. የሕይወት ሕግ የሚሠራው ሲያድግ ብቻ ስለሆነ፣ የሕይወት ሕግ አገልግሎት በሕይወት ማደግን ይጠይቃል—ማር. 4፡3፤ 14፤ 26-29፡-

1. በዙፋኑ ላይ ያለው የክርስቶስ ምልጃ በትንሣኤው ወደ ውስጣችን የዘራውን የሕይወት ዘር ያነሣሣዋል—ዕብ. 7፡25፤ ሮሜ 8፡34።

2. በከበረው እና ከፍ በተደረገው ማንነቱ ሙሉ በሙሉ ዘልቆ ሁለንተናችን ውስጥ እስኪገባ ድረስ ወደ መንፈሳችን ውስጥ የዘራው ሕይወት ያድግ፣ ይዳብር እና የውስጥ ክፍሎቻችንን ሁሉ ፈጽሞ ይሞላ ዘንድ የበኩሩ ልጅ እየማለደልን ነው።

3. መለኮታዊው ሕይወት በውስጣችን ሲያድግ ሳለ፣ ብዙዎች የተካተቱበት መገለጡ እንሆን ዘንድ እንደ እግዚአብሔር በኩር ልጅ የክርስቶስን መልክ ቅርጽ ሊሰጠን፣ ሊያስመስለን፣ የሕይወት ሕግ ይሠራል፤ የሕይወት ሕግ ስህተት ከመሥራት አይቆጣጠረንም፤ የሚቆጣጠረው የሕይወትን ቅርጽ ነው—ቁ. 2፣ 29፦

ሀ. በውስጥ የሚያድረው ዋና ሞዴል፣ የእግዚአብሔር በኩር ልጅ የራሱን መልክ ሊያስመስለን፣ "ልጅ" ሊያደርገን፣ እንደ የሕይወት ሕግ ሰው በማይቆጣጠረው መንገድ በውስጣችን ይሠራል፤ እያንዳንዳችንን ከበኩሩ ልጅ ጋር አንድ አይነት ለማድረግ ጌታ በጉጉት እየሠራ ነው።

ለ. ይህንን ዋና ሞዴል በብዛት ለማራባት የሆነው የእግዚአብሔር መንገድ ሕያው ዋናውን ሞዴል፣ የበኩሩን ልጅ ወደ መላው ማንነታችን ውስጥ መሥራት ነው፤ ከዚህ ድንቅ ዋና ሞዴል ጋር ከተባበርንና ከተከፈትንለት፣ ከመንፈሳችን እየወጣ ወደ ነፍሳችን ውስጥ ይሰራጫል።

ሐ. ደረጃውን ለጠበቀው አርአያ፣ ለእግዚአብሔር በኩር ልጅ ብዙዎች ለተካተቱበት ርቢ እና መገለጥ እንደ አዲሱ ሰው አካሉን ለማቀናበር ብዙ ወንድሞቹ ለሆኑት ለእግዚአብሔር ብዙ ልጆች መራባት የበኩሩ ልጅ ምሳሌ፣ ደረጃውን የጠበቀው አርአያ ነው—ቁ. 29።

4. የሕይወት ሕግ በዋናነት ማድረግ የሌለብንን ነገር በመንገር አሉታዊ በሆነ መንገድ አይሠራም፤ ይልቁንም፣ ሕይወት ሲያድግ ሳለ፣ ቅርጽ በመስጠት፣ ማለትም፣ የክርስቶስን መልክ በማስመሰል የሕይወት ሕግ አዎንታዊ በሆነ መንገድ ይሠራል፤ በሕይወት ሕግ አገልግሎት በኩል፣ ሁላችንም የበሰሉ የእግዚአብሔር ልጆች እንሆናለን፣ እግዚአብሔርም አጽናፍ-ዓለማዊውን፣ ብዙዎች የተካተቱበትን መገለጡን ያገኛል።

## IV. "እኔም አምላክ እሆንላቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑልኛል"—ዕብ. 8፡10፤ ኤር. 31፡33፦

ሀ. እግዚአብሔር አምላካችን መሆኑ ማለት እርሱ ርስታችን ነው ማለት ነው—ኤፌ. 1፡14፡-

1. እግዚአብሔር ሰውን እርሱን መያዝ እንደሚችል ዕቃ አድርጎ ፈጠረው (ዘፍ. 1፡26-27፤ ሮሜ 9፡23-24)፤ ስለዚህ፣ የአንድ ዕቃ ይዘት ርስቱ እንደሆነ፣ እግዚአብሔር የሰው ርስት ነው።

2. እግዚአብሔር ርስታችን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ለድርሻችን የሆነ የጽዋችን እድል ፈንታም ጭምር ነው (መዝ. 16፡5)፤ በኢዮቤልዩ ሰው ወደ ርስቱ በመመለሱ እንደተመለከተው (ዘሌ. 25፡10፤ ሉቃ. 4፡18-19፤ 15፡17-24፤ ሐዋ. 26፡18፤ ቆላ. 1፡12)፣ መዳን ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ መምጣት እና እርሱን እንደ ርስታችን እንደ አዲስ መደሰት ነው።

3. እግዚአብሔር መንፈስን የሚሰጠን እንደ ርስታችን ዋስትና ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ከእግዚአብሔር እንደምንወርሰው ነገር ቅድመ-ቅምሻም ጭምር ነው (2 ቆሮ. 1፡22)፤ ወደ ዘላለም ውስጥ እስክንገባ እና እግዚአብሔር እንደ ሙሉ ድሰታችን እስኪኖረን ድረስ የመንፈስ መያዣነት ጥቂት በጥቂት ብዙ እግዚአብሔርን ወደ ውስጣችን ይጨምራል።

ለ. የእግዚአብሔር ሕዝብ መሆናችን ማለት ርስቱ ነን ማለት ነው—ኤፌ. 1፡11፣ 14፣ 18፤ 3፡21፡-

1. ለድሰታችን ርስታችን የሆነውን እግዚአብሔርን የምንወርስ ብቻ ሳይሆን (1፡14) ነገር ግን ለድሰታው የሆንን የእግዚአብሔር ርስትም ጭምር እንሆናለን (ቁ. 11)።
2. ወደ የእግዚአብሔር ርስትነት እየተቀናበርን ያለነው እግዚአብሔር ውስጣችን በመሥራቱ ነው፤ ይህ ልውጠት ነው፣ በተጨማሪም ውስጠ-ልምምዳዊ መቀደስ ነው።
3. እግዚአብሔር በእኛ ላይ የተለየ ምልክት ለማድረግ ቅዱሱን መንፈስ እንደ ማኅተም በውስጣችን አስቀምጧል (ቁ. 13)፣ ይህም የእግዚአብሔር መሆናችንን ያመለክታል፤ ይህ ማኅተም ሕያው ነው፣ እስከ ሰውነታችንም ቤዛነት ድረስ በእግዚአብሔር መለኮታዊ ንጥረ-ነገር እኛን ለመሙላት እና ለመለወጥ ይሠራል።
4. ሲጠናቀቅ፣ የእግዚአብሔር እና የሰው የጋራ ርስት ለዘላለም በቅዱሳን ያለ የእግዚአብሔር ርስት ይሆናል (ቁ. 18)፤ ይህ በአጽናፍ-ዓለም እና ለዘላለም ከፍተኛው ዘላለማዊው መገለጡ ይሆናል (ራእ. 21፡11)።

**V. "እያንዳንዱም ጐረቤቱን እያንዳንዱም ወንድሙን፡- ጌታን እወቅ ብሎ አያስተምርም፣ ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉ ያውቁኛልና"—ዕብ. 8፡11፤ ኤር. 31፡34፡-**

ሀ. የሕይወት አገልግሎት በውስጣዊው የሕይወት መንገድ እግዚአብሔርን እንድናውቅ ያስችለናል፤ በውስጣችን ባለው የመለኮታዊው ሕይወት ስሜት፣ ንቃተ-ሕሊናዊ ግንዛቤ በሆነው በሕይወት ስሜት፣ ውስጠ-ልምምዳዊ በሆነ መንገድ ከውስጥ እግዚአብሔርን ማወቅ እንችላለን—ሮሜ 8፡6፤ ኤፌ. 4፡18-19፤ ፊልጵ. 3፡10፡-

1. የሕይወት ስሜት የሚመጣው ከመለኮታዊው ሕይወት (ኤፌ. 4፡18)፣ ከሕይወት ሕግ (ሮሜ 8፡2፤ ዕብ. 8፡10) እና ከመንፈስ መቀባት (1 ዮሐ. 2፡27) ነው።
2. በአሉታዊ ጎኑ የሕይወት ስሜት የሞት ስሜት ነው፣ በአዎንታዊው ጎኑ ደግሞ የሕይወት እና የሰላም ስሜት ነው—ሮሜ 8፡6፤ ኢሳ. 26፡3።
3. በትክክል እና በስህተት መርህ፣ በሞት መርህ መሠረት ሳይሆን በሕይወት ስሜት መሠረት በሕይወት መርህ መኖር አለብን።
4. ይህ በመልካም እና በክፉ እውቀት ዛፍ መርህ መሠረት ሳይሆን በሕይወት ዛፍ መርህ መሠረት መኖር ነው—ዘፍ. 2፡9።
5. የሕይወት ስሜት በፍጥረታዊው ሕይወት ወይም በመለኮታዊው ሕይወት እየኖርን እንዳለን እንዲሁም በሥጋ ወይም በመንፈስ እየኖርን እንዳለን እንድናውቅ ያደርገናል።

ለ. "እግዚአብሔርን ለማገልገል እና ለእርሱ ለመሥራት፣ ክርስቲያን ከመልካምና ከክፉ እውቀት ዛፍ መራቅን መማር አለበት...የሕይወትን ዛፍ የሚነኩ ብቻ ሕይወታቸው እና ሥራቸው በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ቀርቶ ያዩታል" (*Messages Given during the Resumption of Watchman Nee's Ministry,* vol. 1, pp. 94-95)።

**VI. በመጨረሻ፣ የዘላለማዊ ኢኮኖሚውን ግብ—አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን—ለመፈጸም ተመላኪነቱን ሳይጨምር በሕይወት፣ በባሕርይ፣ በመገለጥ እኛን እግዚአብሔር በማድረግ ግብ፣ ያለሰው ቁጥጥር እንደሚሠራው የመለኮታዊው ሕይወት ሕግ፣ የሕይወት መንፈስ ሕግ በውስጥ የሚያድረውን መንፈስ መደሰታችን በክርስቶስ አካል ውስጥ እና ለክርስቶስ አካል ነው—ሮሜ 8፡2፣ 28-29፤ 12፡1-2፤ 11፡36፤ 16፡27፤ ፊልጵ. 1፡19፤ ተዛ. ገላ. 4፡26-28፣ 31።**

*© 2020 Living Stream Ministry*